# የ2000 ሺ ዓመት ምሕረት እዮቢልዩ
# የዘመን መስወጫ በዓልንና አዲሱን ሚሊኒየም በማስመልከት
# ብፁዕ አባታችን አቡነ ብርሃነየሱስ ሱራፌል ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን
# ለምእመናን ያስተላለፉት መልእክት፡፡

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ክቡራን ምዕመናን፡

በሩቅና በቅርብ ያላችሁ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ

ክቡራን የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና በጎ ፍቃድ ያላችሁ ሰዎች በሙሉ

ክቡራትና ክቡራን

> *«ጥበብም ሃይልም የእርሱ ስለሆነ እግዚአብሔር ለዘለዓለም የተመሰገነ ይሁን እርሱ ዓመታትንና ጊዜያትን ያፈራርቃል፡፡» (ትንቢት ዳንኤል 2፣ 20 - 21)*

ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ለ2000 ዓ.ም ኢዮቢልዩ የዘመን መስወጫ በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያልኩ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንና በራሴም ስም መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡

> **«ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘለዓለምም ያው ነው፡፡» (ዕብ፡ 13፡8)**

የዚህን ዓመት የዘመን መስወጫ በዓል በማስመልከት ይህን መንፈሣዊ መልዕክት ሳስተላልፍ ያለፈውን ሁለትሺህ ዓመት በሰላም አስፈጽሞን ወደ ሦስት ሺህኛው ሚሌኒየም በደህና አድርሶ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ በዓሉን ለማክበር ላበቃን ቸሩ አምላካችን ምስጋና ይድረሰው እላለሁ፡፡

እነሆ ዘመነ ሉቃስን ጨርሰን ወደ ዘመነ ዮሐንስ እየተሸጋገርን ነው፡፡

የዘመናት ባለቤት የሆነው ቅዱስ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን ነገር ስናስብ በጣም ያስደንቀናል ምክንያቱም እርሱ የዘመናት ብቻ ሳይሆን የሕይወት፣የጥበብ፣የደስታም ምንጭ ነው፡፡

«እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ስለሆነና ፍቅሩም ዘላለማዊ ስለሆነ፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፡፡ እርሱ ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮች ማን ቈጥሮ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡» (መዝ.106 1-2)

ቤተክርስቲያናችን ይህን የዛሬውን አዲሱን ክፍለዘመን ለመቀበል የሦስት ዓመት ቅድመ ዝግጅት ማድረጓ የሚታወቅ ነው፡፡ ለዚህም እግዚአብሔር በሰላም አስጨርሶን ለዚህች ዕለት ስላበቃን ክብርና ምስጋና ለቅድስት ሥላሴ ይሁን፡፡

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ አሁንም ዘወትርም ለዘላለምም ይሁን፡፡

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካዘጋጀልን ነገሮች ሁሉ ታላቁ ጊዜ ነው ፤ በመሆኑም ለጊዜ የሚመጣጠን ዋጋ የለም፡፡ ስለዚህም ያለፈውን ጊዜ መመልከት የሚመጣውንም ወደ ዛሬ ማቅረብና መምራት የምንችለው ዛሬ ባለንበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ የሦስትሺህኛው ዘመን መጀመሪያ እያንዳንዳችን የሕይወት ለውጥ እንድናደርግና የተሰጠንን ጊዜ እንድንሠራበት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቃድና ፍላጎት ነው፡፡ እኛም ራሳችንን እግዚአብሔር ለሚወደው መልካም ሥራ የተገባን በማድረግ ወደ እርሱ በመቅረብ ላደረገልን ነገር ሁሉ ምስጋና ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይገባናል፡፡

ከሚሌኒየሙ በዓል መጀመሪያ እስከ መዝጊያው ድረስ የሚካሄዱ ቤተክርስቲያናችን ለእምነቷ ተከታዮች ያወጣቻቸው የተለያዩ ፕሮግራሞች ለላሉ ምዕመናን እንደ እስካሁኑ በያሉበት ተግባራዊ እንደሚያደርጓቸው ሙሉ እምነቴ ነው፡፡

በዚህ የአዲሱ ሚሌኒየም መላው ሕብረተሰብ እጅ ለእጅ ተያይዞ አገራችንን ከድህነት ከበሽታና ከረሃብ ለማላቀቅ አዲስቷን ኢትዮጵያ በመፍጠር ለመጭው ትውልድ ጥሩ መሠረት እንደሚጥል ፅኑ ተስፋ አለኝ፡፡

በቅርቡ ከምርጫ 97 ጋር ተያይዞ ስታሠሩ እሥረኞች መንግሥት ባደረገው ይቅርታ ቤተክርስቲያናችን ከፍተኛ አድናቆት ያላት ሲሆን ይህንንም ለማስፈፀም ከፍተኛ ጥረት ያደረጉትን የሀገር ሽማግሌዎችን በቤተክርስቲያናችን ስም ላመሰግናቸው እወዳለሁ:: በመሆኑም በአገሪቱ የሚታየው የሰላም የይቅርባይነትና የመቻቻል መንፈስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አደራ እንላለን::

ይህ በሺህ ዓመት አንድ ጊዜ የሚመጣውን የሚሌኒየም በዓል ስናከብር ልናደርገው የሚያስፈልገን ትልቁ ሥራ በኤች አይቪ /ኤድስ/ በሽታ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ሕፃናትን፤ ቤተሰቦቻቸውን ያጡ ወገኖችንና የጎዳና ተዳዳሪዎችን በከፍተኛ የበጎ አድራጎት መንፈስ እራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ በማሰብ በተለመደው የርኅራኄ እርዳታ መርዳት እንደሚገባን አሳስባለሁ:: ህብረተሰቡም በዚህ የሦስተኛውሺህ ዘመን ጅማሬ ራሱን ከኤች አይቪ /ኤድስ/ በመጠበቅ ያለፈውን ስቃይና ሞት በመግታት በእግዚአብሔር ዘንድ ክቡር ስሆነው ሕይወቱ ትኩረት ይሰጥ ዘንድ አስገነዝባለሁ:: እግዚአብሔር ይህን አዲሱን ክፍለ ዘመን በቸርነቱ ስለሰጠን ቀጣዩ ትውልድም ፈሪሃ እግዚአብሔርና መልካም ሥነ ምግባር ያለው ይሆን ዘንድ ቤተክርስቲያንና መንግሥት ተግተው ሊሠሩ ይገባል::

በአዲሱ ሚሌኒየም ምክንያት በአገራችን እየተካሄዱ ያሉትን የልማት ሥራዎች፣ የትምህርት መስፋፋት፣የጤና አገልግሎት መስፋፋት እንዲሁም ልዩ ልዩ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችንና የመልካም አስተዳደር ራዕያችንንና ዕቅዳችንን እግዚአብሔር ይባርክልን:: እኛም በመቻቻልና በመከባበር መንፈስ በህብረት በመነሳሳት ለአገራችን እድገትና ብልጽግና እንሥራ:: ሚሌኒየሙ የምህረት የእርቅና የሰላም እንዲሁም የልማት ጊዜ እንዲሆንልን እንጸልይ::
እንዲሁም በሆስፒታሎችና በየቤቱ በደረሰባችሁ ሕመም ስምትሰቃዩት ሁሉ ምህረቱን ያውርድላችሁ::

- በየማረሚያ ቤቶች ውስጥ ሆናችሁ ይህን በዓል የምታከብሩትንም እግዚአብሔር በምህረቱ ፍታችሁ::
  - በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች ከቤተሰቦቻችሁ የራቃችሁትን ለሀገርና ለወገን መከታ መሆን ግዳጃችሁን ለምትወጡ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ መልካም የሁለት ሺህ ዓመት ኢዮቢልዩና የሚሌኒየም በዓል ይሁንላችሁ::

በድጋሚ አዲሱ 2000ሺህ ዓመት ምሕረት
የሰላም፣ የጤና፣ የደስታና የብልጽግና በዓል
ይሁንልን!! አሜን::